## ፓኖራማ ቁጥር 90

**የትዝብት አድማስ**

ግንቦት 28 ቀን 2002 ዓም

# ለአዲሱ የትግል ምዕራፍ መዘጋጀት

ወያኔ÷ እራሱ ጠፍጥፎ ባነኮረው ምርጫ ÷ እራሱ ፈትፍቶ ራሱ መዋጡን ሰሞኑን ለአባላቱ ገልጿል ። ይህ እንደሚሆን ደግሞ ÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ÷ የፖለቲካን ሀ ሁ በቅጡ የማይገነዘበውም ጭምር እንኳን በቅድሚያ ተንብዮቶት ነበር ። ትላንት መንግሥቱ ኀይለ ማርያም ምርጫ አካሂጄ 98ነጥብ አራት ከመቶ 98.4% አሸነፍኩኝ ብሎ እንደቀለደው ሁሉ የዛሬዎቹ የዘረኛ አምባገነን ሥርዓት አራማጆች ደግሞ ÷ 99 ነጥብ 9 ከመቶ 99.9% አግኝተን ተመረጥን ብለው እየቀለዱ ናቸው፡፡ በሁለቱም አምባገነን ሥርዓቶች መካከል ያለው የፖለቲካ ቆማር ልዩነት÷ መለስ÷ መንግሥቱን በአንድ ነጥብ ሁለት ከመቶ 1.2 % ስሌት መብለጡ ብቻ ነው፡፡ መንግሥቱ ኀለይ ማርያምን በአንድ ነጥብ ሁለት በሆነ ብልጫ በማሸነፉ÷ መለስ ዜናዊ በመስቀል አደባባይ ጥይት በማይበሳው የብረት አጥር ውስጥ ተሸሽጎ " ምድረ- አበሻ ሁሉ ሰራሁልሽ " እያል ሲያሾፍ ተደምጧል ። መለስን በማጀብ በምርጫው የተወዳሩትን የወያኔ ጋሻ ጃግሬዎች አሰተዋዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ "አይናችሁን ለአፈር" ብሎ ያቋመጧትን የፓርልማ ደመዎዝ እንኳን እንዳያገኙ ዕድል ነፍጓቸዋል ። ሕዝባዊ ፍርዱን ሰጥቷቸዋል ።አልመረጣቸውም፡፡ ሊማሩ የሚችሉም ከሆነ÷ አስተምሯቸዋል ። ይህ ትምህረት ወደፊት ሕዝብን እየከዱ ለሥልጣን ብቻ ለሚሽቀዳደሙ ሁሉ ሕዝባዊ ማስጠንቀቂያ ነው ።ከሦስትና ከአራት መንግሥታት ጋር በርኖስ በመለዋወጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሚያታልሉ ሁሉ ታላቅ ትምህርት ነው ። አንድ ሰው ለሁለት ጌቶች በአንድ ጊዜ ታማኝ ሊሆን አይችልም ። ወይ በዓላማ ጸንቶ የሕዝብና የሀገር ታማኝነትን አስርግጦ መታገል÷ ያ ካልሆነ ደግሞ ኢትዮጵያዊ በኩርናውን ለጭብጥ ምስር ለውጦ ተዋርዶ መኖር ! እየኖሩ ከመሞት ይልቅ እየሞቱ መኖር የሚሻለውም ለዚህ ነው ።በዘረኞች አምባገነን ሥርዓት ተገዥ ከመሆን ይልቅ የዕለት ሞቴን ይሰጠኝ ብሎ የቀረጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኮራበታል ! ይመሰገናልም !

ይህ ክስተት የሚያሳየው ቁም ነገር ቢኖር÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማን ምን እንደሆነ የሚያውቅ መሆኑን ነው ። በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ-ዓመት መገባደጃ የነበረ አንድ የማኅበራዊ ኑሮ ጠበብት ተናገረ እንደተባለው ከሆነ “ ማነኛውም ኅብረተስብ የሚባውን መንግሥት ያገኛል ” ሆኖ ነው መሰል ÷ ከወያኔ ጋር ለመወዳደር ተሰልፎ የነበረው ሁሉ የሚገባውን አግኝቷል ። መለስ ዜናዊም÷ በምርጫው ብትሸነፉም እንኳ ÷ የደጀጠኝነት ጠባያችሁን ካሳመራችሁ÷የሥልጣን ፍርፋሬ አይነፈጋችሁም እያላቸው ነው ። ያ ካልሆነ ደግሞ ዕድላችሁ ከርሸሌ እንደሚሆን አትዘንጉ ብሎ አስፈራርቷቸዋል ። ይህ ሁኔታ ÷በወያኔ ምርጫ 97 አንጀቱ የተቃጠለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእጃችሁን አገኛችሁ እያላቸው ነው ። ምክንያቱም በ97ቱ ምርጫ÷ሲያምናቸው ከድተውት ለዕልቂት ስለዳረጉት ነው ። ዕውነት ÷ ጊዚያዊ ሽንፈት ሊያጋጥማት ቢችልም÷ የማታ ማታ ዕውነት ይረታ የሚለው ብኂል እንደሚፈፀም ግን ማንም ሊጠራጠር አይችልም።

መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ይህን 2002 ዓም ምርጫ እነርሱ በፈለጉት መንገድ እንዲገባደድ ለማድርግ ከፍተኛ ዝግጅት እያደረጉ ÷ ሌሎች ተወዳዳሪዎችን ግን እንደ አሮጌ ታኒካ ሲጫወቱባቸው እንደነበር ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰወረ አልነበረም። እኛም ይህን ሁኔታ በመከታተል በወቅቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማሳወቅ ያቅማችንን ሁሉ ስለአደረግን ወደዚያ ዝርዝር ለመመልስ አንሻም። ከዚህም በቀር÷ አስቀድመን ተናግረን ነበር ማለት ÷ የከንቱነት መግለጫ ምፀት ነው ብለን ስለምናምን ወደዚያ አናመራም።

ወያኔ ይህን ምርጫ ለማሸነፍ ያልበጠሰው ቅጥል÷ያልተረጨው ጠበል÷ያልፈነቀለው ድንጋይ ÷ ያልዘየረው አባይ ጠንቋይ አልነበረም ። የ97ቱ ምርጫ ማጭበርበር ያስከተለው ሕዝባዊ አመፅ እንዳይደገም በመፍራት÷ ዳግመኛ ሊከሰት ይችላልና አስፈላጊውን ቅደመ ዝግጅት ማድርግ እንዳለበት ወሰነ። ለዚህም መሰናዶ የሚሆነውን ሁሉ አደረገ ። ከአንድ ዓመት በላይ የወሰደ ስልጠና በማድረግ÷ በሃምሳ ሽ የሚገመት አዲስ የፌዴራል ፖሊስና የአደጋ መከላከያ ልዩ ጦር አሰልጥኖ አሰማራ ። የሕዝቡን አመፅ ለማዳፈን የተዘጋጀው ይህ ፈጥኖ ደራሽ ሠራዊት የሚታጠቀውን ዘመናዊ መሳሪያ በግዥና በዕርዳታ ከቻይና አስመጣ ። የጥይት መከላከያ በርኖስ÷ የጋዝና የውሃ መርጫ መሳሪያዎችንም ብዙ ሚሊዮን ዶላር ወጭ አድርጎ አስመጣ ። የስለላና የመረጃ አቅሙን ለማጠንከር ከሁለት ምዕራባውያን ሀገሮች አስፈላጊውን ትብብርና ርዳታ ማግኘቱን አረጋገጠ ። የአድማ በታኝ ፈጥኖ ደራሽ ሠራዊት በከፍተኛ የተጠንቀቅ ማዘኛ ጠቢያዎች አሰማራ ። ይህንን ሁሉ ዝግጅት አድረጎ ÷ ካበቃ በኋላም÷ ምናልባት በአደጋ ላይ ሊወድቅ የሚችልበት አዝማሚያ ሊከሰት ይችላል በሚል ፍርሃት ÷ይህ ዘረኛ ሥርዓት በዳግም ምፅዓት የሚቀጥልበትን መንገድ ለማረጋገጥ ሲል÷ እንደ በአማራጭ የሚጠቅም ዕቅድ ( Contingency Plan )

አዘጋጅቶ ተቀዋሚ ድርጅቶችን ውኻዅንብር ውስጥ አስገብቶ ፥ የቀቢፀ-ተስፋ ሰለባዎች አደረጋቸው፡፡ ለዚህ ተግባር ዓይነተኛ ሚና የተጨወቱት ሰየ አብረሃና ግብሩ አስራት በመድረክ ውስጥ የከናወኑት የድራማ ተውኔት ነው ፡፡ እንኝህን የቀድሞ የወያኔ አመራር አባላት፥ ጠንካራ ተቃወሚ መስለው እንዲታዩና በሌሎች ላይ የትጠቅ አስፈችነት ተልዕኳቸውን በሚገባ እንዲያከናዉኑ ተደርጓል፡፡ ገሚስ አበላ ባዮችና ገሚስ የዋኅ ፖለቲከ ኞችም በበኩላቸው፥ “ ለእነ ሰየ ዕድል እንስጣቸው ” የሚል ዝማሬ ሲያቀነቅኑ ቆይተዋል፡፡ ምናልባት በአሁኑ ወቅት የክፍለ ሀገሩን ስም መጥቅስ ተገቢ ባለመሆኑ እንዲሁ በአርምሙ እንለፈው እንጅ፥ ወያኔ ወደዚህ አካባቢ በመሄድ ፥ **“ እናንተ እንድትመርጡን እኛም የናንተን ፍላጎት በሙሉ ልብ ለመፈጸም ቃል እንግባ ”** በማለት ከትቂት ምዕመናን ጋር በአንድ ቤተክርስቲያን የቃለ- ማሃል ስምምነት ማድረጉ በመረጃ የተደገፈ ሀቅ ብቻ ሳይሆን ፥ የአደባባይ ምሥጢር ሆኖ ሰንብቷል ፡፡ የወያኔ ቅደመ-ዝግጅት በዚህ ብቻ አላበቃም ፡፡ የተወሰኑትን ታማኝ ተቃወሚዎቹን በማስፈራራት፥**“ የሥነምግባር ስምምነት ሰነድ ”** እንዲፈርሙ አስደርጎ ፥ በመገናኛ ብዙሃን ቀርበው ለመለስ ዜናዊ እጅ እንዲነሱና በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት የሀፍረት ማቅ ለብሰው እንዲናቁ አድርጓቸዋል ፡፡ ይህ ድርጊት መላውን የሀገሪቱ ዜጎች አንገት ያስደፋ እንደነበር ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዜና መዋዕሉ መዝገቦታል ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ የጠላውንና የናቀውን ሰው እንኳንስ ለሀገር መሪነት ቅርቶ ፥ የተበለበትን ዳስ እንዲያፈርስለት እንኳን አይመርጠውም ፡፡ በመሆኑም ፥ ከወያኔ ጋር ለምርጫ የቀረቡትን ሁሉ ስለናቃቸው አልመረጣቸውም ፡፡ እነ መልስ ዜናዊም ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ፥ የተጠሉም የተናቁም መሆናቸውን በሚገባ ስለሚረዱ ፥ ኃይልንና ማጭበርበርን፥ ውንብድናንና ሌብነትን ተጠቅመዉ የምርጫ አቸናፊዎች ነን ብለው አውጀዋል ፡፡ ኢትዮጵያም በአንድ ፓርቲ አምባገነን አገዛዝ ስር መውደቋ እንደገና ተረጋግጧል፡፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕምነት ከሆነ፥ የወያኔ የግንቦቱ ምርጫ ቲያትር፥ እንደ ተበላ ዕቁብ ነው ፡፡ በመሆኑም፥ በፈርስ ላይ የሚያጓጉሩት የወያኔ ቁስለኞች ማጓጎራቸውን ይቀጥሉ እንጅ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ለአዲስ የትግል ምዕራፍ እየተዘጋጀ እንደሆነ መታወቅ አለበት፡፡ የዴሞክራሲ ሥርዓት መስርቶ ሉዓላዊነቱን እስከሚያረጋግጥ ድረስም የትግል ቱማታውን እያጋለ ይቀጥላል፡፡

የውጭ ወራሪዎችንም ሆነ፥ የውስጥ አምባገነኖችን መስዋዕት እየከፈለ ነፃነቱንና መብቱን ያስከበረ ሕዝብ የወያኔን የተጭበረበረ ምርጫ አሜን ብሎ ተቀብሎ አርፎ ይቀመጣል አይባልም ፡፡ ለአውነተኛው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፥ ለፍትኀ-ርትዕ ፥ ለሰብዓዊ መብት፥ ለህግ የበላይነት ፥ ለዕድገትና ብልፅግና ፥ ለአንድነትና ዕኩልነት መታገሉን ይቀጥላል ፡፡ ለዚህም የአሁኑ የሀገራችን የፖለቲካ መልከዐ-ምድር ሁኔታውን አመቻችቶለታል ፡፡

የዕውነተኞቹ ተቀዋሚ ጎራ ተለይቶ ታውቋል። የኃይሎች አስላለፍ እንደ ፀሀይ ብርሃን ፍንተው ብሎ ታይቷል ። ወያኔን አምርሮ የሚታገለውና አስመሳይ ለመጥማጣው ተፈርጇል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ወዳጁንና ጠላቱን በይበልጥ ለይቶ የሚያውቅበት ዕድል አግኝቷል ። እስካሁን ድረስ በአመዛኙ ፥ በስመ ተቀዋሚነት፥ ምርቱን ከግርዱ፥ ፍሬውን ከገለባው ተለይቶ የማይታወቅበት ሁኔታ ነበር ። ትሻልን እየሰደዱ ትብስና የማምጣት አባዜ በብዛት እየተከሰተ ቀጥሏል ። እስቲ ለዚህኛው ደግሞ ጊዜና ዕድል ሰጥተን እንየው የሚባሉ እንዝህላልነትና ትጠቅ አስፈች ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ቀይተዋል ። በግልፅና በድፍረት አካፋን አካፋ ማለት ይገባል። በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ ሊሆን ከቶ አይችልም ። ተቃዋሚ ኀይሎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ፍርድ ሸንጎ በግልፅ እየተገመገሙ ነጥረው መውጣት አለባቸው ። አርበኛን እየገደሉ ፥ ባንዳን እያነገሱ የመቀጠሉ ሁኔታ ማክተሙን በዚህ በግንቦቱ ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ በወሰደው ውሳኔ አረጋግጧል ። እውነተኞቹ ተቃዋሚ ኀይሎችም ማንነታቸውን በይበልጥ ሊያስመሰክሩ የሚችሉበት ዕድል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተሰጥቷቸዋል ። ሕዝባዊ መልዕክትና ሀገራዊ ጥሪ ተላልፎላቸዋል ። የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ማዕከል ያደረገ የትግል ትብብር በመፍጠር ወያኔን ማስወገድ የሚችሉት ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሸንጎ ማንነታቸውን አስመስከረው ታአማኒነታቸውን ያስረገጡ እንደሚሆኑ ማንም ዜጋ አይጠረጥርም ። በመሆኑም ይህ አዲስ የትግል ምዕራፍ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተደግፎ በአርዕድ አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ አመፅ ሕዝባዊ ድል እንደሚያስገኝ የታሪክ ሀቅ ነው ። ኢትዮጵያ ሀገራችን በአምባገነኖች የውሸት ምርጫ ዙሪያ እየተሽከረከረች የምትገዛበት ዘመን ያከትማል ። ለዚህ ደግሞ ፍቱን መድኀኒቱ በዓላማ ፀንቶ የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ መታገል ብቻ ነው ።